# ለሂዩማን ራይትስ ዎች የተሰጠ ምላሽ

**(ክፍል ሁለት)**

በገነነው አሰፋ
(ትርጉም በእስኬው ዚ.)
07-03-2014

*በክፍል አንድ "ሂዩማ ራይትስ ዎች" የተባለው ድርጅት  በኢትዮጵያ ላይ በተደጋጋሚ የሚያሰማውን የተዛባ ወቀሳና ውንጀላ በተመለከተ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠታችን፣ ቀሪውንም በዚህ ክፍል እንደምንቀጥል ቀጠሮ ይዘን መለያየታችን ይታወቃል። በዚሁ መሰረት ክፍል ሁለት እንደሚከተለው ቀርቧል።*

የኢትዮጵያ መንግስት የዜጎችን ሰብዓዊ መብት የማስከበር ግዴታውን በመወጣት ረገድ ካስመዘገበው አበረታች ውጤት ጎን ለጎን አገሪቱን ከድህነት ለማውጣት በገባው ቃል መሰረት ህብረተሰቡን በየደረጃው ተጠቃሚ ያደረገ ልማት በማምጣት፣ የዓለም አቀፉ እርዳታ ሰጪ ማህበረሰብ ከጠበቀው በላይ ውጤት ማምጣት ችሏል። ይሁን እንጂ የዘመናችን የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ይህን ገሀድ እውነታ መመልከት ተስኗቸዋል፤ ለምን?

እርግጥ ነው፤ እነዚህ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ይህን እውነታ ለማየት ያልቻሉት የኒዮ-ሊበራሊዝም ርዕዮተ ዓለም አራማጅ በመሆናቸው ነው፤ በሚከተሉት የኒዮ-ሊበራሊዝም ርዕዮተ ዓለም ሳቢያ ስለሰብዓዊ መብት ፅንሰ ሃሳብ ያላቸው ዕይታ ጠቧል። በመሆኑም፣ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ዋነኛ ራዕይና ግብ ምን እንደሆነ ለመረዳት አለቻሉም። ይህ ደግሞ አብዛኛዎቹ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የመሰረተ ልማት አውታሮች መስፋፋት የሰብዓዊ መብት አያያዝን በማሻሻል ረገድ የላቀ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት እንዳይታያቸው ጋርዷል። ይህ ግርዶሽ በፈጠረም ችግር ምክንያት እውነታውን አለመገንዘባቸው ሳያንስ፣ በዓላማችን ያሉ ልማታዊ መንግስታት በሙሉ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችንና መሰረታዊ የሰው ልጅ የነፃነት መብቶችን እንደማይቀበሉ አድርገው ነው የሚመለከቷቸው።  ለዚህ የጅምላ ፍረጃቸው ዋነኛው ምክንያት የልማታዊ መንግስታት መንግስታዊ አደረጃጀታቸውም ሆነ

የሚከተሉት መርህ ከኒዮ-ሊበራል መንግስታት የተለየ በመሆኑ ነው። እነዚህ የለዮ-ሊበራል መንግስታት የልማታዊ መንግስታትን እንቅስቃሴ በዓይነ ቁራኛ እንደሚከታሉት ሁሉ፣ እነዚህ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችንም በተለየ ዓይን ነው የሚያይዋቸው።

ምንም አንኳን ማጋነን ቢመስልም የኢትዮጵያ መንግስት ከተለመዱት ልማታዊ መንግስታት የተለየና እውነተኛው የልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ሞዴል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ምክንያቱም በኢኮኖሚ የዳበሩት ታላላቅ የእስያ ልማታዊ መንግስታት ከተከተሉት መርህ የተለየ የልማት ሞዴል በመከተሉ ነው እነዚህ አገራት በልማታዊ መንገድ ተጉዘው ድህነትን ከቀረፉ በኋላ የዴሞክራሲ ጉዟቸውን 'ሀ' ብለው የጀመሩት። የኛ ግን እነሱ የልማት መንገድ ከጀመሩበት ሂደት በተለየ አኳኋን ገና ከጠዋቱ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታውን ጀምረን ይህንኑ በልማታዊ መንገድ እያጠራና እያጠናከረ መሄድን የመረጠ ስርዓት ነው። ልማታዊ መንግስታችን ገና ከአጀማመሩ በዴሞክራሲ ጎዳና ለመራመድ ብዙሀነትን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለማስተናገድ መወሰኑ ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ፈጣን ልማት እውን ለማድረግ ተችሏል።

እዚህ ላይ ልብ ልንል የሚገባው እነዚህ የኒዮ-ሊበራል አቀንቃኞች አንድ ጊዜ “ኢትዮጵያ የመበታተን አደጋ ላይ ናት” በሌላ ጊዜ ደግሞ “ኢትዮጵያ ከአቅሙ በላይ በሚያልም አፋኝ አምባገነናዊ ገዥ ፓርቲ የምትመራ ሀገር ናት” የሚለውን አስተያየት የሚሰጡት ሀገራችን የምትገኝበትን ሁኔታ በትክክል የሚገልፅ መረጃ ስለሌላቸው አለመሆኑን ነው፤ እኛ ከልመና እንዳንወጣና በነሱ መዳፍ ውስጥ ተጨብጠን ስንለምን እንድንኖር ከመፈለግ እንጂ። ይህ ብቻ አይደለም፣ እነዚህ ወገኖች “የህዝብን መሠረታዊ ፍላጎቶችና መብቶች ለማሟላት ማውጣት የሚገባትን በጀት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቁ ፕሮጀክቶች ላይ እያፈሰሰች ነው” ሲሉም የኢትዮጵያን መንግስት ሲኮንኑ ይደመጣሉ። ይህ የመከራከሪያ ነጥባቸው ግን የኢትዮጵያ መንግስት የሚሊኒየሙን የልማት ግቦች በማሳካት ረገድ በተከታታይ ዓመታት አስደናቂ ውጤት ከማስመዝገቡና በድህነተ ቅነሳ ስትራቴጂ የተቀመጡ ግቦችን በማሳካት ፕሮግራሙን ከሚተገብሩ አገራት መካከል በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ በመሆን የዕዳ ስረዛ የተደረገለት ከመሆኑ አንፃር ስንመዝነው ክሳቸው ሁሉ ሚዛን የሚደፋ ሆኖ አናገኘውም። እዚህ ላይ መረሳት የሌለበት ዋነኛው ነጥብ የ”ሚሊኒየም የልማት ግቦች”ን ማሳካት የሰብዓዊ መብት አያያዝን በማሻሻል ረገድ ፈጣን ለውጥ የሚያመጣ መሆኑ ነው።

በህብረተሰቡ አሳታፊ የዕቅድ ዝግጅትና የትግበራ መርህ እንዲፈፀም የተዘጋጀውን የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም በመተግበር ረገድ አገራችን ያሳየችው ውጤታማ አፈፃፀም የሚሊኒየም የልማት ግቦችን በማሳካት ረገድ የተሻሉ ውጤቶች እንዲመዘገቡ ትልቅ እገዛ አድርጓል። እዚህ ላይ ሂዩማን ራይትስ ዎችን ትዝብት ላይ የሚጥለው እስከዛሬ በኢትዮጲያ ላይ ባወጣቸው ዘገባዎች የኢትዮጵያ መንግስት ህብረተሰቡን ያሳተፈ ልማት በማካሄድ ለዜጎች ሰብዓዊ መብት መከበር ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የተሻለ የሰብዓዊ መብት አያያዝ ለማስፈን ስለሚያደርገው ጥረት አንዳችም በጎ ነገር የለም ብሎ የማያውቅ አለመሆኑ ነው። እነሱ ምንም ይበሉ ምን የኢትዮጵያ መንግስት  የሚያካሂዳቸው ፈጣን የመሰረተ ልማት አውታሮች የመገንባት፣ የሰብዓዊ መብትን ለማክበርና ለማስከበር የላቀ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ተቋማትን የማቋቋምና የማጠናከር ሥራ የሕብረተሰቡን ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር አድግጓል።

ይህም ብቻ አይደለም ሂዩማን ራይትስ ዎች እስከዛሬ የኢትዮጵያን ሰብዓዊ መብት አያያዝ አስመልክቶ ባወጣቸው ዘገባዎች የኢትዮጵያ መንግስት በራሱ ተነሳሽነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሰብዓዊ መብቶች ማክበርም ሆነ ማስከበር ጋር ተያያዥነት ያለው ሥራ ለሚሰሩ የመንግስት ተቋማት በሙሉ ስለ ሰብዓዊ መብት መርሆዎችንና እሴቶች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን አንዴም እንኳ ጠቅሶ አያውቅም፤ ለምሳሌ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም የህግ አስፈፃሚ አካላትና የእስር ቤት አስተዳዳሪዎች፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ስለሰብዓዊ መብት እሴቶች፣ ህጎች፣ አዋጆችና የተግባር መመሪያዎች አስመልክቶ በሚዘጋጁ ሥልጠናዎች ላይ የመሳተፍ ግዴታ አለባቸው። እያንዳንዱ ሰልጣኝ  በህገ- መንግስቱና በተለያዩ አዋጆች ለተደነገጉ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችንና የሥራ አስፈፃፀም መመሪያዎች ታጋዥ ባይሆን (ቢጥስ) ተጠያቂ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ሌላው ጉዳይ፣ ምንም እንኳን ሂዩማን ራይትስ ዎች በሪፖርቱ አንስቶት ባያውቅም፣ ከሰብዓዊ መብት ጋር ተያያዥነት ያለው ሥራ የሚሰሩ ዋና ዋና የመንግስት መ/ቤቶች በመደበኛነት ከሰብዓዊ መብት ጋር በተያያዘ ስለሚያከናውኑት ተግባር በዓመታዊ ዕቅዳቸው ውስጥ ያካትታሉ።

እነዚህ ተቋማት በዕቅድ አፈፃፀም ያስመዘገቡት ስኬትና ያጋጠማቸው ውድቀት በየተቋማቱ በሚደረግ ግምገማ ይፈትሻል፣ ከዚህ በተጨማሪ በአገር አቀፍ ደረጃ የሰብዓዊ መብት አያያዝን ዘላቂነት ባለው መልኩ ለማሻሻል እያንዳንዱ ተቋም እ.ኤ.አ በ2010-2015 ዓ.ም

ለማሳካት በአገራችን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ ከተቀመጡት የሰብዓዊ መብት አያያዝ ግቦች አንፃር በመቃኘት ዓመታዊ የድርጊት መርሃ ግብር ይነድፋል። ይህ የተቀናጀ ዕቅድ የአገሪቱን የሰብዓዊ መብት አያያዝ ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር የሚከናወን መሆኑ ግን እነ ሂዩማን ራይትስ ዎችን በመሳሰሉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ዓይን ውስጥ እንደማይገባ ጥርጥር የለውም፤ ይልቁንም የሂዩማን ራይትስ ዎች እና መሰሎቹ በወልቃይት የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድብ ፍንዳታ ሲባል በአካባቢው ነዋሪ የነበሩ ሰዎች ተፈናቅለዋል ሲሉ የኢትዮጵያ መንግስትን ይከሳሉ። እነዚህ ደርጅቶች ከሰብዓዊ መብት ጋር በማያያዝ በኢትዮጵያ ላይ የሚያካሂዱትን ውንጀላ ከእነዚህ የልማት ፕሮጀክቶች ጋር ያያዙት ያለምክንያት አይደለም። የኒዮ-ሊበራሊዝም ርዕዮት አቀንቃኝ የሆኑት የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ፖሊሲ አውጪዎች መንግስት መራሽ ከሆነ የማህበረ-ኢኮኖሚ ዕድገት ለውጥ ጋር ተያይዞ ለሚተገበር ማንኛውንም ዓይነት ፕሮግራም ሆነ ፕሮጀክት ጥላቻ ስላላቸው ነው። በዚህም ኢትዮጵያ በምታካሂደው የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫ ግድብ ግንባታ ሳቢያ ግንባታው ከመጀመሩ በፊት በቦታው ይኖር ያልነበረ ስፍር ቁጥር የሌለው ህዝብ ተፈናቅሏል ሲሉ የአዞ እንባ እያነቡ የሀሰት ውንጀላቸውን እውነት በማስመሰል መጮሃቸው ምስክር ነው።

ከዚህ በተጨማሪም የ5 ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ፍሬ የሆነውን የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ መጠናቀቅን ተከትሎ በወልቃይት ኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድብ ግንባታ ሳቢያ ተፈናቀለ ከሚሉት በላይ ህዝብ ሊፈናቀል ይችላል የሚል ስጋት እንዳላቸው በመግለጽ ክሳቸውን የበለጠ ተደማጭ ለማድረግ ይጮሃሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች ኢትዮጵያ በምታካሂዳው የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ሳቢያ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተፈጽሟል እያሉ የሚያሰሙት ጩኸት መንግስት መራሽ የልማት፣ ዕድገትና በሰብዓዊ መብት መከላከል ያለውን አዎንታዊ መስተጋብር ከማይቀበለው ርዕዮተ ዓለማዊ አቋማቸው የመነጨ መሆኑን ለመሸፈን ነው፡፡

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ፍትሃዊ ልማት የአገሪቱ ብቸኛ የሆነውን ሀብት ማለትም መሬት፣ ውሃና የሰው ጉልበት በአግባቡ ጥቅም ላይ ከማዋል ውጭ እውን ሊሆን አይችልም፡፡ ከዚህ ውጭ ሕዝቦችን በእኩልነት ተጠቃሚ የሚያረግ ፍትሃዊ ልማት ማምጣት የማይታሰብ ነው፡፡ በሌላ አባባል ሀገሪቱ ያላትን የተፈጥሮና የሰው ሃብት ከማልማት ውጭ በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደረውን የአገሪቱን አብዛኛው ህዝብ የማህበራዊና

የኢኮኖሚ ልማት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት መገንባትም አይቻልም፡፡ ሆኖም የዜጐችን የሰብአዊ መብት በማስከበር ረገድ ይህ ነው የሚባል ለውጥ አላመጣችም በሚሉት በእነዚህ ወገኖች ዘንድ ኢትዮጵያ ያላትን የተፈጥሮና የሰው ሃብት በማልማት የዜጎችን መሠረታዊ ፍላጐቶች ለማሟላት የምታደርገው ጥረት እንደ ከንቱ ልፋት ነው የሚታየው፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚመራባቸው ፖሊስዎች የተዋቀሩባቸውን መሠረታዊ መርሆዎች ስንመለከት ዕድገትና ሰብዓዊ መብቶች ርስ በርስ ተመጋጋቢና ሊነጣጠሉ የማይችሉ ብቻ ሳይሆን አንደኛው ለሌላው ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ፅምር እንረዳለን፡፡ በርግጥ ዕድገትና ሰብአዊ መብቶች የማይነጣጠሉና ርስ በርስ ተመጋጋቢ መሆናቸውን የሚያሳየው ፅንሰ-ሃሳብ በዓለማችን ተቀባይነት ያገኘው እ.አ.አ በ1968 በኢራን-ቴህራን በተካሄደው የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ ላይ ነበር፡፡ ይኸው ጉባኤ ባወጣው የአቋም መግለጫ ሰነድ ላይ እንደተመለከተው አንድ ሀገር የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን በመተግበር ረገድ ዘላቂነት ያለው ለውጥ የማምጣት ጉዳይ፤ ውጤታማ የሆነ አለም አቀፋዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት ፖሊስዎችን ቀርፆ በመተግበር በኩል ባላት ስኬት ላይ ይወሰናል፡፡ የኢህአዴግ መንግስትም ከዚሁ በመነሳት የሂዩማን ራይትስ ዎች ኢትዮጵያ በሁሉም መስክ ለውጥ ማምጣት የቻሉ ፖሊሲዎችን እየተገበረች መሆኗና ከዚህም ያገኘችውን መልካም ፍሬ በሚገባ ሳይረዳ፣ የአገሪቱ የሰብአዊ መብት አያያዝ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን የጣሰ ነው ሲል የሚያሰማው ጩኸት ተአማኒ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም ብላ ታምናለች፡፡

በኢትዮጵያ ህገመንግታዊ ሥርዓት ዋነኛ የማእዘን ድንጋይ ከሆኑት መርሆዎች መካከል የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች ዋነኛው ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በአገሪቱ የዜጐች ሰብአዊ መብት ባልተከበረበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ህዝቦች በተለያዩ መልኮች የልማት ተጠቃሚ ለመሆን ችለዋል ብሎ አስተያየት መስጠት ከእኩይነት የመነጨ ነው ባይባል እንኳን ተአማኒነት የጎደለው መሆኑ እሙን ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂነት ባለው መልኩ የሕዝቦችን መሠረታዊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፍላጐቶች ለማሟላት ያስቻለ ልማት ማምጣት የተቻለው ሕዝቦችን በማስገደድና በመቆጣጠር ሳይሆን ሕዝቦች የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት እንዲሆኑና በልማቱ መስክ በፈቃዳቸው ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ በመቻሉ ነው፡፡

ነገር ግን ይህን በሚቃረን መልኩ ነው - በሕዝብ ተሳትፎ ፈጣን ልማት እያስመዘገበ ያለውን የኢን የኢትዮጵያ መንግስት የሚወነጅሉ ጣቶች እየተቀሰሩ ያሉት፡፡ እነዚህ ወገኖች የኢትዮጵያ መንግስትን የሚወነጅሉበት ዋነኛው ምክንያት እነሱ እንደሚሉት የኢትዮጵያ መንግስት የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችንና መርሆዎችን በሥራ ላይ ለማዋል ባለመቻሉ ሳይሆን ኢትዮጵያ ሰብአዊ መብትን ከልማት ጋር በማስተሳሰር የምትከተለውን የፖሊሲ አቅጣጫ ስለማይወዱት ነው፡፡ ለዚህ ነው የኢትዮጵያ መንግስት የሰብአዊ መብት አያያዝ የእኛን ይሁንታ ካላገኘ ዋጋ የለውም ብለው የሚያስቡት፡፡

ሌላው የሂዩማን ራይትስም ሆነ መሰሎቹ ሊገነዘቡት የሚገባው ጉዳይ በዓለማችን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች በመተግበር ረገድ በዋነኛነት ሁለት ዓይነት የአፈጻጸም ስልቶች ተግባራዊ እየተደረጉ መሆኑን ነው፡፡ አንደኛው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር የሰብዓዊ መብት እሴቶችና መርሆዎች በየአገሪቱ የሕግ፣ የፖለቲካ፣ የርዕዮተ ዓለም እና ማህበራዊ አስተሳሰብ ውስጥ መስረጽና መካተት አለበት የሚለውና ይህንኑ መርህ መሠረት ያደረገው የም ራባውያኑ የአፈፃፀም ስልት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በዓለም አቀፉ ደረጃ ተቀባይነት ያገኙት የሰብአዊ መብት መርሆዎች የእያንዳንዱ ሀገር ማኅበረሰብ ለሕይወት ከሚሰጠው ትርጉም ጋር በእጅጉ የተቆራኘ በመሆኑ የየአገሪቱን ታሪካዊ ልምድና ባህላዊ እሴቶች ባገናዘበ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ የተሻለ ውጤት ይመጣል የሚለው ከምዕራቡ ዓለም ውጭ ያሉ አገራት የሚያራምዱት የአፈፃፀም አቅጣጫ ነው፡፡ ሂዩማን ራይትስ ይህን አያውቅ ይሆናል፡፡

ኢትዮጵያ ለሕግ የበላይነት የላቀ ከበሬታ ያለው የበርካታ ሞራላዊ እሴቶች ባለቤት የሆነ ሕዝብ ካላቸው ከምዕራቡ ዓለም ውጭ ካሉ አገራት መካከል አንዷ ናት፡፡ የአገራችን ህዝቦች በረጅም ዘመን ታሪካቸው ያዳበሯቸው ለሰው ልጆች ሕይወትና ሰብአዊ መብቶች የላቀ ክብርና ዋጋ የሚሰጡ ባህላዊ እሴቶች ባለቤት ናት፡፡ ከዚህ አኳያ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገራት ማህበረሰቡ በዘመናት ታሪኩ ያዳበራቸውን ለሰብአዊ መብት የላቀ ዋጋ የሚሰጡ ሀገር በቀል ባህላዊ እሴቶችን ከዘመናዊ የሰብአዊ መብቶች ፅንሰ-ሃሳቦችና የአፈፃፀም ተሞክሮዎች ጋር አዛምዶ መተግበር በሀገር አቀፍ ደረጃ የሰብአዊ መብት አያያዝን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

እዚህ ላይ አፅንኦት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ የሰብአዊ መብቶችን የማክበርና የማስከበር ጉዳይ የመንግስትን ቁርጠኝነት ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡን የአመለካከት ለውጥ እና መብቱ ሲጣስ ለመብቱ መከበር የሚታገል ማህበረሰብ መፍጠርን የሚጠይቅ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ለሰው ልጆች ሕይወትና ሰብአዊ ክብር ያላቸውን ባህላዊ እሴቶች ከግምት ያስገባ የአፈፃፀም አቅጣጫ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያረግ እሙን ነው፡፡

እነ ሂዮማን ራይትስ ዎች ከዘሁ ጋር በተያያዘ ልብ ሊሉት የሚገባው ዋነኛው ነጥብ ለሰው ልጆች ሕይወትና ለሰብዓዊነት ክብርና ዋጋ የሚሰጡ ባህላዊ  እሴቶች መሠረት ያደረገ የሰብአዊ መብት የአፈፃፀም ስልት ተፈላጊውን ውጤት ለማምጣት ዋነኛ መሣሪያ መሆኑን ነው፡፡

በኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ እነዚህ ለሰብአዊ መብቶች መከበር የላቀ ዋጋ የሚሰጡ ባህላዊ እሴቶች ተጥሰው ኢሰብአዊነት የነገሰው ከ1966—1983 ዓ.ም በቆየው የደርግ የአገዛዝ ዘመን ነበር፡፡ የ1966 አብዩትን ተከትሎ ሕዝቦችን በጅምላ በመጨፍጨፍ ሥልጣኑን ያፀናው ጁንታው የደርግ መንግስት አገሪቱን ያስተዳደረበት 17 የስቃይና መከራ ዘመን የሰው ልጆች ሕይወት ዋጋ ያጣበት፣ ኢሰብአዊነት የነገሰበት እና የሕግ የበላይነት የተጣሰበት ክፉ ዘመን ነበር፡፡ ይህ የአሁኑ ዘመን በአገራችን ኢሰብአዊነት የበላይነትን ይዞ ከቆየበት ረጅም ዘመን አንፃር ሲታይ አጭር ጊዜ ቢሆንም በነዚያ ክፉ ዘመናት በሰው ልጆች ላይ የተፈፀመው ግፍና ጭካኔ ወደፊት እንዳይደገም፣ በወቅቱ ኢሰብዓዊ ድርጊት የፈፀሙ የመንግስት ባለሥልጣናት . . . በሕግ እንዲጠየቁ ተደርጓል፡፡

ይህ የተደረገው ማንም ሰው የመንግስት ሥልጣን ያለአግባብ በመጠቀም ለሚፈጽመው ሕገወጥ ተግባር ከተጠያቂነት እንደማያመልጥ ለአሁኑና ለመጪው ትውልድ ትምህርት ለመስጠት ነው፡፡ ከዚሁ ጐን ለጐን እንደ ደርግ የመንግሥት ሥልጣንን በመጠቀም ተመሳሳይ ወንጀል እንዳይፈፀም ለዜጐች ሰብአዊ መብቶች መከበር ሕጋዊ ዋስትና የሚሰጥ ህገ-መንግስታዊ ሥርዓት እውን ሆኗል፡፡ እንግዲህ የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ሕገመንግስቱ ውስጥ እንዲካተት ቀዳሚ ሚና የተጫወተው ከደርግ ውድቀት በኋላ የመንግሥት ሥልጣን የያዘው የፖለቲካ ፓርቲ (ኢህአዴግ) ነው፡፡ ይኸው

የፖለቲካ ፓርቲ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን በሕገመንግስቱ ውስጥ በማካተት ለዜጎች ሕገ-መንግስታዊ ዋስትና ከመስጠቱም በተጨማሪ በሕገ-መንግስቱ ዋስትና የተሰጣቸው የዜጎች ሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችና አዋጆች በትክክል መተርጐማቸውን የሚከታተል ከፖለቲካም ሆነ ከማንኛውም አካል ተፅዕኖ ነፃ የሆነ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን እንዲቋቋም አድርጓል፡፡

እንግዲህ እነ ሂዮማን ራይትስ ዎች የመንግሥት ሥልጣንን ተገን በማድረግ በዜጐች ላይ ስለሚፈፀም ሕገ ወጥ የሰብአዊ መብት ጥሰት ኢህአዴግን እናስተምርህ የሚሉት ድርጅቱ በደርግ መንግስት የተካሄደው የሽብር ተግባርና ሕገወጥ አገዛዝ ዳግም በታሪካችን እንዳይከሰት በቁርጠኝነት የታገለ መሆኑን በመርሳት ነው፡፡

የኢህአዴግ መንግስት የመንግሥት ሥልጣንን ተገን በማድረግ በዜጐች ላይ ስለሚፈፀም ሕገወጥ ተግባር በሚገባ የሚያውቀው በመሆኑ ምንም ዓይነት ትምህርትም ሆነ ገለፃ አያስፈልገውም፡፡ ለእውነት እንነጋገር ከተባለ ከልክ ያለፈ የሰብዓዊ መብት ጥሰት በሚካሄድበት አገር የፖለቲካ መረጋጋት ማስፈንም ሆነ ልማትን ዕውን ማድረግ እንደማይቻል ማነው ኢህአዴግን ሊያስተምር የሚችለው? ላስተምር ቢልም ከድካም የዘለለ ፋይዳ አይኖረውም - ምክንያቱም ለኢትዮጵያ ገዢ ፓርቲ የዜጐችን ሰብዓዊ መብት የማክበርና የማስከበር ጉዳይ አገሪቱን እንዲያስተዳድር ይሁንታውን የሰጠውን ሕዝብ ህይወት ለማሻሻል በቁርጠኝነት እያደረገ ያለው ትግል ዋነኛ አካል በመሆኑ ነው፡፡

ይህ ሲባል ግን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት አያያዝ ፍፁም ነው ማለት አይደለም፡፡ የሀገሪቱ መንግሥትም የሰብዓዊ መብት አያያዝን አስመልክቶ ፍፁም ነኝ፣ ምንም ጉድለት የለብኝም ብሎ አያውቅም፡፡ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢም በአገራችን የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የሚፈፀሙባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉ ያምናል፡፡ በርግጥ እነዚህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የሚፈፀሙባቸው አጋጣሚዎች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ነገር ግን ከዚሁ ጋር ተያይዞ መነሳት የሚገባው ጥያቄ በኢትዮጵያ የሚፈፀመው የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሆን ተብሎ የሚፈፀም ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ አዎ ሆን ተብሎ የሚፈፀም ነው ሲል ማንም የፈለገውን ሊል ይችላል፡፡ እውነታው ግን ያ አይደለም፡፡

ከዚህ አኳያ እስከዛሬ ስለኢትዮጵያ መንግስት በአፅንኦት ያልተነገረው የሀገራችን መንግስት ተቀብሎ የሀገሪቱ ህግ አካል ያደረጋቸውን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶችንና ድንጋጌዎችን በውጭ ኃይሎች ግፊት እውን ይሆናል የሚል እምነት እንደሌለው ነው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም - መንግስት የሂዩማን ራይትስ ዎች በኢትዮጵያ ላይ ያዋጣኛል ብሎ የሚከተለው የስም ማጥፋት ስትራቴጂ አዎንታዊ ውጤት ያመጣል ብሎ አያስብም፡፡ በርግጥ የኢህአዴግ መንግስት እነዚህ ወገኖች በሚያራምዱት የስም ማጥፋት ስትራቴጂ ተደናግጦ ይበጀኛል የሚለውን የሰብዓዊ መብት የአፈፃፀም ስልት ተግባራዊ ከማድረግ ወደ ኋላ ብሎ እንደማያውቅ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት በዚህ ረገድ ካለው የማያወላውል አቋም አንፃር የውጭ ሃይሎች በኢትዮጵያ ላይ በኃይል ጫና ለማሳደር የሚከተሉት ስትራቴጂ በራሱ የተሸነፈ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ይህን ስንል የኢትዮጵያ መንግስት የውጭ አገራት በሰብዓዊ መብት አያያዝ ረገድ ለሚያደርጉለት ድጋፍ አድናቆት የለውም ማለታችን ግን አይደለም፡፡ ይልቁንም የኢትዮጵያ መንግስት በሀገሪቱ ህገ-መንግሥት ላይ የተቀመጡ ቃል ኪዳኖችንና ትልሞችን እውን ለማድረግ የሚያደርገውን ጥረት ለማገዝ የሚደረግለትን ማንኛውም ዓይነት ድጋፍ በደስታ ነው የሚቀበለው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የሀገራችን ፖሊሲ አውጭዎችም ከእንከን የፀዳ ነው በማይባለው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት አያያዝ ላይ የሚሰነዘረውን ህጋዊ አግባብነት ያለው ቅሬታና ትችት ለመቀበል ፈቃደኛ ናቸው፡፡ የአገራችን ዋነኛ ውሳኔ ሰጪ አካላት በእጅጉ እያስከፉቸው ያለ ጉዳይ ካለም ለሰብዓዊ መብት መከበር ቆመናል የሚሉ ወገኖች አገሪቱ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎችን ለማክበር የገባቻቸውን ግዴታዎች አልተወጣችም በሚል ሽፋን የኢትዮጵያን መልካም ገፅታ በሚያበላሽ መልኩ በሚያወጡት የውንጀላ ዘገባዎች ነው፡፡

የእነዚህ ኃይሎች ሌላው አስገራሚ ነገር በአንድ በኩል ራሳቸውን ዋነኛ የዓለም አቀፉ ሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች አስከባሪ አድርገው በማየት ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ የገባቻቸውን ግዴታዎች እንድታከብር ግፊትና ጫና የሚያረጉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሁሉም አስተዳደራዊ ዘርፎች የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከምትካፈልበት ዓለም አቀፍ መድረክ ለማግለል ያለማቋረጥ የሚታክቱ መሆናቸው ነው፡፡

ሂዩማን ራይትስ ዎች ከቆመለት ዓላማ ጋር በሚቃረን መልኩ የሚያካሂዳቸው እነዚህ ጣልቃ ገብነቶች በኢትዮጵያ ላይ በሚያወጣቸው የሰብዓዊ መብት ጥሰት የውንጀላ ዘገባዎች ውስጥ ተካተዋል፡፡ እነዚህን ጣልቃ ገብነቶች በኢትዮጵያ ላይ በሚያወጣቸው የውንጀላ ዘገባዎች ውስጥ ያካተተው ያለምክንያት አይደለም - ምንም ይሁን ምን አንድ ውጤት ያስገኝልኛል ብሎ በማሰብ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም እንዳሰበው ምንም ውጤት አላስገኘለትም፡፡

በአጠቃላይ የሂዩማን ራይትስ ዎችና መሰሎቹ ከሰብዓዊ መብት ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ላይ በተደጋጋሚ የሚሰነዝሩት ውንጀላ ከእውነት የራቀና በተጨማሪ ማስረጃም ያለተደገፈ መሆኑን ስንመለከት በኢትዮጵያ መንግስት ላይ የሚያካሂዱት የውንጀላ ዘመቻ በዋነኛነት ያነጣጠረው ህገ መንግስታዊውን ሥርዓት ለመናድ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ለዚህም ሂዮማን ራይትስ ዎች በተደጋጋሚ በኢትዮጵያ ላይ ሽብር ተግባር ለመፈፀም ሌት ተቀን ቀና ደፋ የሚሉትን በውጭ ሀገር የሚኖሩ አክራሪ ተቃዋሚ ሃይሎች የሀሰት ምስክርነትን መሠረት ያደረገ መሆኑን መጥቀስ ይበቃል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ለዚህ ዓይነቱ የሀሰት ዘገባ ተጨንቆ አያውቅም፡፡ ምክንያቱም በእነዚህ ወገኖች ለሚስነዘርበት የሀሰት ውንጀላ መልስ ለመስጠት ከመድከም ይልቅ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ውስጥ ያሰፈረውን ብሔራዊ የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብር ለመተግበር መረባረብ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሰብዓዊ መብት አያያዝና ጥበቃ ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር ሁነኛ ርምጃ በመሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ስፍር ቁጥር የሌላቸው የሃሰት ውንጀላዎች አንድም በዋሽንግተን ከሚኖሩ ቅጥረኛ ፀረ-ኢትዮጵያ አክራሪ ተቃዋሚ ኃይሎች አሊያም አገራችንን ለማፍረስ የቻሉትን ድንጋይ ከመፈንቀል ወደ ኋላ ከማይሉት የኢትዮጵያ ጠላቶች የማያልፍ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ እውነታ በመነሳት የኢትዮጵያ መንግስት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ጥናትን መሠረት ያደረገ ነው ብሎ ያወጣው የሰብዓዊ መብት አያያዝ ዘገባ በእውነተኛ መንፈስ የሀገሪቱን የሰብዓዊ መብት አያያዝ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር ያለመ ሳይሆን በተቃራኒው የቆመ ነው ሲል መፈረጁ አግባብነት ያለው ብያኔ ነው፡፡ ከዚህ በተረፈ ወደፊት የሰብዓዊ መብት አያያዝን አስመልክቶ በኢትዮጵያ ላይ የሚወጡትን ዘገባዎች እውነተኛ ማስረጃዎችን መሠረት ያደረጉና ገንቢ ሚና ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ ተስፋ ከማድረግ በስተቀር ምንም ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም በእውነተኛ ማስረጃ ላይ ያልተመሠረቱ ዘገባዎች የሰብዓዊ መብት አያያዙን ወደ ተሻለ ደረጃ

ለማሸጋገር በቁርጠኝነት ለሚንቀሳቀስ ማንኛውም ወገን ምንም የሚፈይዱት ነገር ባለመኖሩ ነው፡፡